# የልማት ዕቅዱ አፈፃፀምና የ2007 ዓ.ም በጀት

**ጌታቸው ደስታ** 07-24-14

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ በጀት አፅድቃለች–ለ2007 ዓ.ም የበጀት ዓመት። በዚህም የፌዴራል መንግስት የ2007 ዓ.ም በጀት 178 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ሆኖ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል። ይህ በመጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ካለፈው ዓመት በጀት ጋር ሲነፃፀር የ24 ቢሊዮን ብር ብልጫ ያለው ሲሆን፣ ሀገሪቱ የጀመረችውን የህዳሴ ጎዞ የሚያሳልጥ እንደሚሆን ይጠበቃል። ከአጠቃላይ በጀቱ ውስጥ 64 ነጥብ 8 በመቶው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የድህነት ተኮር ፕሮግራሞች (ማለትም ለመንገድ ግንባታ፣ ለውኃ፣ ለትምህርት፣ ግብርና፣ ጤና እና የገጠር ኤሌክትሪክ ፕሮግራሞች) የተመደበ ነው። ይህም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በአግባቡ ለመተግበር ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከበጀቱ ውስጥ ለትምህርት 24 ነጥብ 5 ቢሊዮን እንዲሁም ለመሰረተ ልማት 29 ቢልዮን ብር ተመድቧል። በጀቱ የሀገሪቱን ቀጣይ ዕድገት ለማረጋገጥ መንግስት ለሰው ሀብት ልማትና ለመሰረተ ልማት ያለውን ከፍተኛ ትኩረት የሚያረጋግጥ ነው።

እንደሚታወቀው የሀገራችንን የልማት ደረጃ ለማሻሻልና ድህነትን ለማስወገድ ታላላቅ ተስፋዎችን የሰነቀ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረም አራት ዓመታት አለፈውታል፡፡ ታዲያ በቀጣዩ የ2007 በጀት ዓመት የዕቅዱ ትግበራ የሚጠናቀቅበት ዓመት ይሆናል፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የዕቅዱ አፈጻጸም በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ የልማት ውጤቶች የተመዘገቡበት ነው፡፡ ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስችሉ አቅሞችም ተፈጥረዋል፡፡ በርካታ ተግባራትም የተከናወነባቸው ዓመታት ናቸው፡፡

ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ በነበሩት ሶስት የዕቅዱ የትግበራ ዓመታት የሀገራችን ኢኮኖሚ በአማካይ 10 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በኢኮኖሚው መስክ አጠቃላይ ሀገራዊ የምርት መጠን በእጥፍ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህን ግብ ተግባራዊ በማድረጉ ረገድም መንግስትና ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሰፊ ርብርብ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ታዲያ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካትም ባለፉት አራት ዓመታት በሁሉም መስኮች የተመዘገቡ ውጤቶች አፈጻጸማቸው

ሲታይ ዕቅዱን ማሳካት የሚያስችሉ መሆናቸውን በየወቅቱ መንግስት የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ያስረዳሉ፡፡ መንግስት የነደፈውን የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሀገራችን ስታሳካ አሁን ካለችበት የዕድገት ደረጃ ይበልጥ ወደ ላቀ የልማት ደረጃ የሚያሸጋግር ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲጠናቀቅ ያልተቋረጠ ርብርብ እየተደረገበት ይገኛል፡፡ እኔም በዛሬው ጽሑፌ ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት የተከናወኑ ሰፋፊ የልማት ስራዎችና ለቀጣዩ ዓመት የተያዘው የ178 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በጀት የልማት ትልሞችን ለማሳካት ያለውን ፋይዳ ለማመላከት እሞክራለሁ። አብረን እንዝለቅ።...

እንደሚታወቀው የኢፌዴሪ መንግስት የሚከተለው ፖሊሲና ስትራቴጂ ግብርና መር ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ይህም ግብርናንና አርሶ አደሩን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ ነው፡፡ ታዲያ መንግስት ይህ እንዲሆን የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ አርሶ አደር ከመሆኑም በላይ፤ በቁጥር ሲሰላም ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ሰማንያ አምስት ከመቶ የሚሆነው በገጠር አካባቢ የሚኖርና በግብርና ዘርፍ የሚተዳደር ስለሆነ ነው፡፡

ግብርና የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያ በመሆኑም የሀገሪቱ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ እናም መንግስት ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ አውታር ግብርናን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲና ስትራቴጂ እየተከተለ ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመሰጠቱም ላለፉት አስር ተከታታይ ዓመታት ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማስመዝገብ ችሏል፡፡

እርግጥ በኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ካለው መጠነ ሰፊ ድርሻ የተነሳ የሀገሪቱን ዕድገት በማሳካት ግብርናን የዘነጋ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ የተሳሳተ መሆኑ ከማንም የሚሰወር ጉዳይ አይደለም፡፡ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በቀጣይነት ለማረጋገጥ መንግስት የነደፈውን የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ በቅድሚያ በምግብ ራስን መቻል ያስፈልጋል። ለጥቆም በኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን የግብርና ምርቶችን በማስፋፋት በኢንዱስትሪውና በግብርናው መካከል ያለውን ትስስር ይበልጥ ማጎልበት ይገባል። በመሆኑም መንግስት ይህን አቅጣጫ እየተከተለ ይገኛል፡፡ መንግስት የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነድፎ ወደ ትግበራ ከመግባቱ አስቀድሞ ባለፉት ሰባት ዓመታት የዘረጋቸውን የድህነት ቅነሳና

የልማት ዕቅዶችን በግብርና እና በገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ውስጥ በሚገኙ አቅጣጫዎች የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ሰፊ ጥረት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ከ1996 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ባሉት ሰባት ዓመታት የሀገራችን የግብርና ዘርፍ ስንመለከት በተነጻጻሪ ከዚያ በፊት ከነበረው ዕድገት በእጅጉ የላቀ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የኢፌዴሪ መንግስት የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ በአሁኑ ወቅት ሀገራችን በተግባር ላይ እያዋላቸው ካለው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በፊት ለተከታታይ ሰባት ዓመታት በአማካይ አስራ አንድ ነጥብ ሁለት በመቶ ዕድገት አስመዝግቦ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ከዚሁ ዕድገት ግብርና በዕድገቱ ላይ የነበረውን ድርሻ የተመለከትን እንደሆነ ስምንት ነጥብ አምስት በመቶ ነው፡፡ ለዚህም ነው –በሀገራችን ዕድገት ግብርና ተኪ የሌለው ሚና የሚጫወተው፡፡

እንደሚታወቀው የግብርና ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን ውጤታማነት በተግባር ያረጋገጡ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህ መሰረትም ከ1996 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ግብርና በሀገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ማስመዝገቡ በየወቅቱ ስለ ዕድገት የሚተነብዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በወቅቱ አስደናቂ ግስጋሴ እንደሆነ ሪፖርት አቅርበው ነበር፡፡ የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከመውጣቱ በፊት በነበሩት ሁለት ዓመታት የተመዘገበው ባለ ሁለት የዕድገት አሃዝ መጠን ከጅምሩ ዕቅዱ እንደሚሰምር ማሳያዎች ነበሩ፡፡

እነዚህን ምርኩዝ በማድረግ የግብርና ሴክተር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በግብርና ሰብል ልማትን ፣በእንስሳትና በተፈጥሮ ሀብት ልማቶች አስተዳደር እንዲሁም በአደጋ መከላከልና በምግብ ዋስትና ዘርፎች ላይ ተመስርቶ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእዚህ ውስጥም የሰብል ምርትን ለማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የምግብ ኢንዱስትሪውን ዘርፍ መደገፍ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እንዲካተቱ የተደረጉ ሲሆን፣ አበረታች ለውጦችም እየታዩ ታይተዋል፡፡

የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችም በተመሳሳይ በቅደም ተከተላቸው የ16 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ እና የ11 በመቶ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ የትግበራ ክንውኑ በስኬት ተጠናቅቋል፡፡ ዕቅዱን በተያዘለት የጊዜ ገደብ በድል ማጠናቀቅ ሀገሪቱን ከግብርና መር ስትራቴጂ ወደ ኢንዱስትሪ መር ስትራቴጂ ለማሸጋገር ይቻል ዘንድ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለሆነም

መንግስትና መላው የሀገራችን ህዝቦች ለዕቅዱ ስኬት ሰፊ እንቅስቃሴ ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡ በልማት ዕቅዱ ላይ በትልምነት የተያዙት ዘርፎች በርካታ ሲሆኑ፤ ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው የልማት ዘርፍ የሆነውን የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እያከናወነው ያለውን ታላቅ ሀገራዊ የልማት ስራ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

እንደሚታወቀው ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር መደላድል በመፍጠር እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግለው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነው፡፡ በዚህ ዕቅድ ሂደት ውስጥ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የተረካቢ ሚናነቱ እንዲረጋገጥ በየዘርፉ በግልጽ የተቀመጡ ዕቅዶችን ማስፈጸም የግድ ይላል፡፡ በዕቅዱ መሰረትም በሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ለማስመገብ በዝቅተኛው አማራጭ 11 በመቶ፣ በከፍተኛ የዕድገት አማራጭ ደግሞ 14 ነጥጥብ ዘጠኝ በመቶ ለማስመዝገብ ከተጣለው ግብ ውስጥ ኢንዱስትሪው በየዓመቱ እስከ 20 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግብ ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ (በጊዜው የገበያ ዋጋ) በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 373 የአሜሪካ ዶላር በ2005 ዓ.ም ወደ 550 የአሜሪካ ዶላር ከፍ ብሏል፡፡ በ2003 በጀት ዓመት በተካሄደው የቤተሰብ ገቢ እና የፍጆታ ወጪ ጥናት መሠረት፤ በ2003 ዓ.ም የድህነት ምጣኔ ወደ 29 ነጥብ 6 በመቶ ዝቅ ማለቱን ያመላከተ ሲሆን፤ ምጣኔው በ2005 ዓ.ም ወደ 26 በመቶ ዝቅ እንዳለ ይገመታል፡፡ በጥናቱ ትንታኔ መሠረት በ2005 በጀት ዓመት በተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ከአንድ ሚሊዮን ዜጎች በላይ ከድህነት ወጥተው የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል ችለዋል፡፡

በሌላ በኩልም ዕድገቱ እንዲመዘገብ በተደረጉ በርካታ የምጣኔ-ሃብት እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። በዚህም በኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው ሥራ አጥነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ ለምሳሌ ያህል የከተሞች የሥራ አጥነት ምጣኔ ብንወስድ በ2005 ዓ.ም ወደ 16 ነጥብ 5 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ድህነትን ለማጥፋትና የዜጎችን ኑሮ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ዘርፈ ብዙ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል፡፡ ተግባር ላይ የዋሉት የምጣኔ-ሃበትና ማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች በሀገሪቱ አሰራር መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት መቻላቸው በግልጽ ታይቷል፡፡ በመሆኑም

ባለፉት ዓመታት የዓለም የምጣኔ-ሃብትና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ችግር ላይ በነበረበት ሁኔታ ጭምር ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የተገኘው የምጣኔ ሃብት መሻሻልም ብዙሃኑን ያሳተፈና ተጠቃሚ ያደረገ እንዲሁም የግብርናንና የተፈጥሮ ሀብትን ብሎም የውሃ አጠቃቀምና አያያዝ በማጎልበት ዘላቂ ልማትን ለማምጣት መሰረት የጣለ ነው፡፡ በትምህርትና ጤና ረገድም የተገኙ መሻሻሎች ዜጎችን ለልማት ያነሳሱና ከተገኘው ልማትም ተጠቃሚ ያደረጉ ናቸው፡፡ በመሰረተ ልማት ግንባታው ዘርፍ የተደረጉ ጥረቶችም የገጠሩን ነዋሪ ጭምር ተደራሽ ያደረጉ መሆናቸው የትግባቸው አፈፃፀም ያሳያል፡፡

ከ1994 ዓ.ም ወዲህ መንግስት ፈጣን ልማትን ማምጣት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ልማታዊ የግል ኢንቨስትመትን በማበረታታትና የኪራይ ሰብሳቢነትን አማራጮች ለማጥበብ በግሉ ዘርፍ የማይሰራ የልማት ስራዎችን አከናውኗል። በዚህም ውስን ሀብትን መሰረታዊ ችግሮችን በሚፈታ የልማት ስራዎች ላይ በማዋል፣ የልማቱ ሃይሎችን በማቀናጀትና በመምራት፣ የህዝብ ተሳትፎን በማጎልበት እና የግል ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ፈጣንና ቀጣይነት ያለውና ፍትሃዊ የኢኮሚ ዕድገትንና ማህበራዊ ልማትን ዕውን ለማድረግ ችሏል፡፡

ሆኖም ድህነት አሁንም ዋና ችግር በመሆኑ ዕድገቱ ሰፊ መሰረት ኖሮት እንዲቀጥል የማድረጉ ወሳኝነት አያጠያይቅም፡፡ ለፈጣንና ቀጣይ ዕድገት የግልም ሆነ የመንግስት ኢንቨስትመንት ያለውን ወሳኝ ሚና በመገንዘብ ኢኮኖሚው ውስጥ ኢንቨስትመንት ያለውን ድርሻ በመጠኑ ለማሳደግ ቢቻልም፤ የሀገር ውስጥ የቁጠባ መጠን አነስተኛ በመሆኑ የተፈለገውን ያህል ሊሆን አልቻለም–ያለው መሻሻል እንደተጠበቀ ሆኖ። ዳሩ ግን የሀገር ውስጥ ቁጠባ ዝቅተኛ ቢሆንም የኢንቨስትመንት ምጣኔው አበረታች ነው፡፡

ታዲያ በዚህ የአራት ዓመት የስራ ክንውን ሲታይ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በኢኮኖሚው መስክ አጠቃላይ ሀገራዊ የምርት መጠን በእጥፍ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህን ግብ ተግባራዊ በማድረጉ ረገድም መንግስትና ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሰፊ ርብርብ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ2005 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት እና የሀገር ውስጥ ቁጠባ ምጣኔዎች በቅደም ተከተል 33 በመቶ እና 17 ነጥብ 7 በመቶ ደርሷል፡፡ በዕቅዱ

ከተያዘው ግብ በላይ አፈጻጸም እንዲያሳዩ ማድረግም ተችሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተገኘውን ውጤት ለማስቀጠል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተለይ የቁጠባ ምጣኔ እንዲያድግ በማድረግ የኢንቨስትመንት ፍላጎታችንን በሀገር ውስጥ ፋይናንስ አቅም መሸፈን አቅማችን እየተሻሻለ እንዲሄድ እየተደረገ ነው፡፡

ከዕቅዱ ዋና ዋና ዓላማዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ነበር፡፡ ምንም እንኳን በመጀመሪያዎቹ የዕቅዱ ሁለት ዓመታት የዋጋ ንረት ፈተና የነበረ ቢሆንም፤ በቀሪዎቹ የትግበራ ዓመታት የዋጋ ዕድገቱን በመቆጣጠር በዕቅዱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሳያሳድር እንዲቀጥል ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፣ እየተደረገም ይገኛል፡፡ ዘላቂ መፍትሔዎቹ የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት እና የሀገር ውስጥ የግብይት ሥርዓትን ውጤታማ ማድረግ መሆናቸውም ታምኖበታል፡፡ ከዚህ አኳያ የዘርፉን ተዋንያን ያካተተ የጋራ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ሌላው በዋናነት ሊጠቀስ የሚገባው የዕቅዱ ትግበራ ውጤት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች የተመዘገበው ልማት ስኬት ነው፡፡ በመሆኑም የመሠረተ ልማትን ከማስፋፋትና የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ከማረጋገጥ አንጻር ጉልህ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዚህ መሠረት በመጀመሪያዎቹ ሶስት የዕቅዱ ትግበራ ዓመታት የመንገድ፣ የባቡር፣የኢነርጂ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የውሃና የመሳሰሉት የመሠረተ ልማት አውታር ዝርጋታዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ በርካታ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተፈፃሚ ሆነዋል። አፈጻጸማቸውም በመልካም ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ መካከልም ሀገራዊ የመንገድ ኔትዎርክ እንዲስፋፋ ያደረጉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፤ የሀገሪቱ የመንገድ ሽፋን ከፍተኛ መሻሻል እንዲያሳይ እገዛ አድርገዋል፡፡

እነዚህ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በመሆናቸውም የፌዴራልና የክልሎች መንገዶች ጠቅላላ ርዝመት በ2004 ዓ.ም ከነበረበት 56 ሺ190 ኪ.ሜ፣ በ2005 ዓ.ም ወደ 58 ሺ 338 ኪ.ሜ ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሁሉ አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የተገነቡ የገጠር መንዶች ርዝመት 27 ሺ628 ኪ.ሜ ደርሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚወስድበት ጊዜ በ2005 ወደ 2 ነጥብ አንድ ሰዓት ዝቅ ብሏል፡፡ በባቡር ዝርጋታ ረገድ የተያዙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምም በመፋጠን ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመሠረተ ልማት ግንባታ ሊነሳ የሚገባው

ጉልህ ውጤት የኢነርጂ አቅርቦትን በማስፋፋት ረገድ የተደረገው ጥረት ነው፡፡ የኃይል ማመንጨት አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ገቢራዊ እየሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚጠናቀቁትና ኃይል ማመንጨት የሚጀምሩት በቀጣዮቹ ዓመታት ቢሆንም ቅሉ፣ የፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም በመልካም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መጥቀሱ ተገቢ ነው፡፡ በተለይም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ከፍተኛ የመንግስትና የህዝብ ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት በተያዘለት ዕቅድ መሠረት እየተገነባ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ባለፉት አራት የዕቅድ ዓመታት በሌሎች ዘርፎች ማለትም በመጠጥ ውሀ እና በቴሌኮም አቅርቦት ረገድ የተመዘገቡት አበረታች ውጤቶች ድህነትን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካትም በእነዚህ ዓመታት በሁሉም መስኮች የተመዘገቡ ውጤቶች አፈጻጸማቸው ሲታይ ዕቅዱን ማሳካት የሚያስችሉ ናቸው ማለት ይቻላል–የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃልና።

እርግጥ መንግስት የነደፈው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተሳካ ሀገራችን አሁን ካለችበት የዕድገት ደረጃ ይበልጥ ወደ ላቀ ምዕራፍ ትሸጋገራለች። በማህበራዊ ልማት ረገድም በርካታ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው፡፡ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉና ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህ ረገድ በ2005 ዓ.ም የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን 93 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ በህጻናትና በእናቶች ጤና በኩልም መሻሻል ታይቷል፡፡ በተለይም በህጻናት ጤና ረገድ ሀገራችን የህጻናትን ሞት በሁለት ሦስተኛ በመቀነስ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የተቀመጠውን ግብ ከተቀመጠለት ጊዜ ሁለት ዓመታት ቀድማ ማሳካቷን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማረጋገጡ የዕቅዱን ስኬት አይቀሬነት የሚያረጋግጥ አመላካች ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በትምህርት ዘርፍ የአንደኛ ደረጃ (1-8) ትምህርት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ጨምሮ ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ በ2005 በጀት ዓመት 95 ነጥብ 4 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ ከ17 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ህጻናትም በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሌላው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ነው፡፡ የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆኑ የግል ባለሀብቱ በኢንዱስትሪው ሴክተር በስፋት እንዲሳተፍ ጥረት እየተደረገ

ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱንም ለማፋጠን ይቻል ዘንደ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ የጎላ ድርሻ እንዲጫወት ይፈለጋል። ስለሆነም በሴክተሩ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጡ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ባለፉት አራት ዓመታት ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገው ውጤትም ተገኝቶባቸዋል፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በተደረገው ጥረት ተጠቃለው ሲታዩ፣ አንዳንዶቹን ግቦች አስቀድመን የደረስንባቸው ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚሳኩ መሆናቸውን የሚያመላክት አፈጻጸም ተስተውሏል፡፡ ቀሪዎቹን ግቦች ለማሳካት ደግሞ ከፍተኛ ጥረትና ርብርብ የሚጠይቁና ፈታኝ ሁኔታዎችም የሚስተዋሉባቸው መሆናቸውን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ አቶ ሶፊያን አህመድ በቅርቡ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባደረጉት ማብራሪያ መጥቀሳቸው አይዘነጋም፡፡ ያም ሆኖ ግን በእስካሁኑ የአፈጻጸም ሂደትም ትርጉም ያለው ተጨማሪ የማስፈጸም አቅም መገንባት ተችሏል። የተመዘገቡት ውጤቶችም በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ የልማት ተነሳሽነትንና መነቃቃትን ፈጥረዋል፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የ2006 በጀት ዓመት የዕቅዱ ትግበራ ከመቼውም በላይ ተጠናክሮ ተግባራዊ የተደረገበት ዓመት ነው፡፡ በርካታ ፕሮጀክቶች ወደ መጠናቀቅ የተቃረቡበት፣ በግብርናውም ረገድ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎችና የግብርና ኤክስቴንሽን በማስፋት ስትራቴጂው ተጠናክሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች የበለጠ የተስፋፉበት፣ ለልማታዊ ባለሀብቶች የሚደረገው እገዛም ተጠናክሮ የቀጠለበት፣ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ ሰፋፊ ሥራዎች በተጠናከረ ሁኔታ ገቢራዊ ስለሆኑ የምጣኔ ሃብት ዕድገቱ ቀጣይነት ይረጋገጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

እስካሁን የተገኙት መረጃዎች እንዳሳዩትም በበጀት ዓመቱ ለምጣኔ ሃብቱ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ ባለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ይመዘገባል ተብሎ የተቀመጠው ዕድገት እንደሚሳካ አሳይቷዋል፡፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመኸር የግብርና ሰብል ቅድመ ምርት ዳሰሳ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው፣ በ2006 የበጀት ዓመት 227 ሚሊዮን ኩንታል የአገዳና የብርዕ፣ 21 ሚሊዮን የጥራጥሬ እንዲሁም 6 ሚሊዮን ኩንታል የቅባት እህሎች በድምሩ 254 ሚሊዮን ኩንታል የመኸር ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት ከአርሶ አደር መሬት ይሰበሰባል፡፡ ይህም በ2005 ከተሰበሰበው ጠቅላላ የመኸር ምርት ጋር ሲነፃር የ10 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ በኢንዱስትሪ ዘርፍም የ2006 አፈጻጸም መረጃዎች

እንደሚያመለክቱት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቢሆንም የዘርፉን ከፍተኛ ድርሻ ከሚወክሉት የማኑፋክቸሪንግና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴ ሁኔታ አንፃር ኢንዱስትሪው ፈጣን ዕድገት ያስመዘግባል ተብሎ ይታመናል፡፡ በጥቅሉ በሁሉም ዘርፎች እየታየ ካለው እንቅስቃሴ አንፃር ኢኮኖሚው በ2006 በጀት ዓመትም የ11 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የሚያመላክቱ ሁኔታዎች መኖራቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡

በገቢ አሰባሰብ ረገድም በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያዎቹ አሥር ወራት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ የቀጥታ በጀት ድጋፍና ዕዳ ቅነሳን ጨምሮ 97 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የፌዴራል መንግስት ገቢ ተሰብስቧል። ይህም ከፀደቀው የዓመቱ በጀት የ88 ነጥብ አንድ በመቶ አፈፃፀም ያሳየ ነው፡፡ በተጠቀሱት ወራት ውስጥ ታክስ እና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብቻ 86 ሚሊዮን 221 ሺ ብር ያልተጣራ የፌዴራል መንግስት ገቢ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፤ ከተያዘው በጀት አንጻር የ89 ነጥብ አንድ በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል:: ከዚህ ውስጥም የተጣራ የፌዴራል መንግስት የታክስ ገቢ 79 ሚሊዮን 471 ሺ ብር ነው። ይህም የዓመታዊ ዕቅዱን 79 በመቶ ያህል የታክስ ገቢ መሰብሰብ መቻሉን ያሳያል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት የተጠናከረ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመኖሩ በበጀት ዓመቱ የ11 በመቶ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚመዘገብ ይጠበቃል፡፡

እንደሚታወቀው የ2007 በጀት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትግበራ የሚጠናቀቅበት ነው። የትግበራው እንቅስቃሴ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚካሄድ የሚጠበቅ ሲሆን የ2007 በጀትንም ልዩ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ ይኸው ነው፡፡ ቀደም ሲል በመግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት የ2007 በጀት ዓመት አጠቃላይ የፌዴራል መንግስት ወጪ በጀት 178 ቢሊዮን 565 ሚሊዮን 906 ሺህ 571 ብር (178 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን) ሆኖ ፀድቋል፡፡ ይህ በጀት ከጸደቀው የ2006 በጀት አንጻር የ15 ነጥብ 3 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ከጠቅላላው የወጪ በጀት ውስጥ 45 ቢሊዮን 055 ሚሊዮን 288 ሺ 445 ብር ለመደበኛ ወጪ፣ 66 ቢሊዮን 990 ሚሊዮን 216 ሺህ 931 ብር ለካፒታል ወጪ፣ 51 ቢሊዮን 520 ሚሊዮን 401 ሺህ 195 ብር ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ እና 15 ቢሊዮን ብር ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪዎች መሸፈኛ የተያዘ በጀት ነው፡፡ ከዚህ የፌዴራል መንግስት ጠቅላላ የወጪ በጀት የካፒታል በጀት ድርሻ 37 ነጥብ 5 በመቶ ሲሆን፣ ይህም ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት

የበጀት ድጋፍ ድርሻ ደግሞ 28 ነጥብ 9 በመቶ ሲሆን፣ የመደበኛ ወጪ በጀት እና የምዕተ ዓመቱን ልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪዎች በጀት ደግሞ በየቅደም ተከተላቸው የ25 ነጥብ 2 እና የ8 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡

ከአጠቃላይ የ2007 መደበኛና ካፒታል በጀት ውስጥ 64 ነጥብ 8 በመቶው የተመደበው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የመንገድ፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃ፣ የጤና እና የገጠር ኤሌክትሪክ ፕሮግራሞች ነው፡፡ በመሆኑም በጀቱ ዘላቂ ልማት በማምጣት ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ሚና ባላቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎችና የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ላይ ያመዘነ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን አቅጣጫ በአግባቡ ለመተግበር እንደሚያስችል የሚያመላክት ነው፡፡ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተበጀተው ከፍተኛው የ2007 ዓ.ም በጀት ፋይዳውም ይኸው ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ ይህ የምጣኔ-ሃብት እመርታ ዝም ብሎ የመጣም አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ መላው ህብረተሰብ ምጣኔ ሃብት ለሀገሩ ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ ማወቁና ድህነትን በዋነኛነት ማስወገድ ለመንግስት ብቻ የተተወ አለመሆኑን መገንዘቡና ለተግባራዊነቱም ከዳር እስከዳር በመነቃነቁ የተገኘ ድል ነው። በሀገሪቱ ያለው አስተማማኝ ሰላምም ከዚሁ ጋር የተያይዞ የሚታይ ነው፡፡ ሰላም በኢንቨስትመንት እና በቱሪዝም ዘርፍ ወደ ሀገራችን የሚመጡት የውጭ ዜጎች ትኩረት የሚሰጡት ጉዳይ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለው አስተማማኝ ሰላም ለውጤቱ መገኘት ሌላኛው ተጠቃሽ ጉዳይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የአገልግሎቱ ዘርፍ የተጠነከረ እና ፍትሃዊ አሰራር የነገሰበት እንዲሆን የተከናወነው የመልካም አስተዳደር ስራም ለምጣኔ ሃብቱ እመርታ መገኘት የበኩሉን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ምንም እንኳን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እጅጉን የተለጠጠና ሊሳካ አይችልም የሚል ቅድመ ግምት በርካቶች የሰጡት ቢሆንም፤ በጠንካራ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች የታጀበው የመንግስት የማስፈጸም አቅም እና በህብረተሰቡ የበረታ ክንድ ለተገኘው ውጤት ሰፊውን ሚና ተጫውቷል፡፡ ከዚህ ባሻገርም በቀጣዩ ዓመት የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የሚጠናቀቅበት በመሆኑ፤ አሁን የተገኘው የምጣኔ ሃብት ዕድገት ግለቱን ጠብቆ እንዲጓዝ ብርቱ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም መንግስት የመደበውን ከፍተኛ በጀትና የህዝቡን ፈርጣማ ክንድ ይበልጥ

በማስተባበር በአራት ዓመቱ አፈፃፀም ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበባቸው ዘርፎችን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣ ትኩረት የሚሹትን ደግሞ አጠናክሮ በመቀጠል የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ ዳር ማድረስ ይገባል። ህዝብን የያዘ ሃይል የማይወጣው አስቸጋሪ ዳገትና የማይወርደው ፈታኝ ቁልቁለት የለምና። አበቃሁ።